# ኢሬቻ— የኦሮሞ ህዝብ ባህልና ወግ ማለጫ!

ቶሎሳ ኡርጌሳ 09-27-17

በያዝነው ወር የኢሬቻ በዓል በደመቀ ስነ ስርዓት ይካሄዳል ተብሎ ይጠበቃል። በዓሉ የኦሮሞ ህዝብ ባህልና ወግ ማለጫ ነው። ከፖለቲካዊ ጉዳዩች ጋር የሚያያይዘው አንዳችም ነገር የለም። እናም በዕለቱ ይህን በዓል ለማክበር የሚወጣው የኦሮሞ ህዝብ እንዲሁም በበዓሉ ላይ የሚገኝ ታዳሚ ስለ ሰላም፣ መቻቻልና አንድነት ለፈጣሪው ምስጋና በማቅረብ ለሰላማዊ አከባበሩ መትጋት የሚኖርበት ይመስለኛል።

አንዳንድ ፅንፈኞችና ለሀገራችን ሰላም በጎ የማይመኙ ሃይሎች ባለፈው ዓመት በዓሉን ተገን በማድረግ እኩይ ዓላማቸውን ለማራመድ ሲሞክሩ ተስተውሏል። በወቅቱ በነበረው ትርምስም በሰላማዊ መንገድ በዓሉን ለማክበር የወጡ ወንድሞቻችን ህይወት አልፏል። አካልና ንብረትም ወድሟል።

ይህን የበዓሉን ፈጣሪ ማላመኛነት በመተው የፖለቲካ ማራመጃ ለማድረግ የሞከሩት ፅንፈኞች በወቅቱ የፈጠሩት እንዲህ ዓይነቱን አጥፊ ተግባር እንጂ ለህዝቡ ምንም ዓይነት የፈየዱለት ነገር የለም። ወትሮም ፅንፈኞች ተግባራቸው የህዝብን ሰላምና ሚረጋጋት ማወክ በመሆኑ ከዚህ በላይ የሚጠበቅ ነገር የለም።

ያም ሆኖ የዚህ ፅሑፍ ዓላማ ኢሬቻ የኦሮሞ ህዝብ ባህልና ወግ ማለጫ እንዲሁም ፈጣሪን ማላመኛ መሆኑን ማሳየት ስለሆነ ወደዚያው እዘልቃለሁ። እንደሚታወቀው የኦሮሞ ህዝብ ከጥንት ጀምሮ ከሚያከብረው በዓላት ወስጥ አንዱ ኢሬቻ ነው። ይህ የሰላም በዓል ማንኛውም የኦሮሞ ተወላጅ በላቀ ሁኔታ አምላኩን ያማስግንበታል። አምላኩ ለስህተት፣ ለደባ፣ ለተንኮልና ለወሸት ትዕግስት የሌለው መሆኑን ያስባል።

ይህ አምላክ በሰማይና በምድር ያለውን ማናቸውንም ነገር ፈጥሮ የሰው ልጅ እንዲጠቀምባትና እንዲያዝበት ስልጣን ስለሰጠው፤ ለዚህ ሁሉ የማይነጥፍ አምላካዊ ስጦታውና ለተደረገለት ሁሉ የኦሮሞ ህዝብ ምስጋና የሚያቀርብበት ቀን ነው—የኢሬቻ በዓል። ስማንም እየጠራ 'እንኳን ከክረምት ወደ ፀደይ በሰላም አደረስከን' እያለ ተዓምራቱን ከፍ የሚያደርግበትም ታላቅ ዕለት ነው።

በዓሉ በሁሉም የኦሮሞ ተወላጅ ልብ ወስጥ ሰፊ ስፍራ አለው። ከክረምት ወደ ፀደይ በሚደረገው ሽግግር፤ ክረምት በፀደይ ተተክቷልና ደስታ ይገለፃል።

የክረምቱ የጨለማ ጉም ተገፎ በብርሃን ተተክቷልና ደማቅ ብርሃን ይታያል። የፀደይ ፀሐይ ያለ ምንም ስስት በማሉ አቅሟ ልግስናዋን ትቸራለችና ህይወት የደመቀች ትሆናለች።

የኦሮሞ አርሶ አደር የዘራው እህል ፍሬ ሊያፈራ በአበባ ደምቆ ሌላው ደግሞ እያሸተ ነውና በተስፋነት ይመስላል። በክረምቱ ዝናብ ሳቢያ የጨቀየው ሜዳ በፀደዩ መግባት እየደረቀ ነውና ሁሉም ከየቀየው ብቅ ብሎ የሰላም ቄጠፄማን የሚያነጥፍበት ወቅት ይሆናል።

እናም ይህ ሰንሰለታዊ ክንውን በሁሉም የኦሮሞ ተወላጅና ባህሉን በሚያከብሩ የሀገራችን ወንድሞቹ ዘንድ በየዓመቱ ፀደይ ትወስታው ከታላቅነቱ ጋር አብሮ ወልብ ይላል— የኢሬቻ በዓል።

በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ በከፍተኛ አክብሮትና ስነ ስርዓት በየዓመቱ ማስከረም ወር ላይ የሚከበረው "የፀደይ ኢሬቻ" እና ሜጨው በልግ ሲገባ የሚከበረው "የበልግ ኢሬቻ" በዓል የዘህ ኩሩና ጨዋ ህዝብ ወግና ባህል ማለጫ ብቻ ነው። እናም በፖለቲካ ጉዳዮች ማጠለፍ የለበትም።

በዓሉ በሰላማዊ መንገድ እንዲካሄድ መንግስት የራሱን በቂና አስተማማኝ ዝግጅት የሚያደርግ ቢሆንም፤ ህብረተሰቡም በዓሉ በአንዳንድ የህዝብን ሰላም በሚሹ ሃይሎች ድብቅ የተላላኪነት አጀንዳ እንዳይወል መካላከል ያለበት ይመስለኛል።

ይህን የምለው ከምንም ተነስቼ አይደለም። ባለፈው ዓመት በህዝባችን ላይ ፅንፈኞች የፈጠሩትን አሳዛኝ ተግባር ተመርኩዤ ነው። እንደምናስታወሰው አምና እነ ጃዋር መሐመድን የመሳሰሉ የውጭ ሃይል ተላላኪ ፅንፈኞች በበዓሉ ላይ ሁከት ፈጣሪዎችን በሚደራጅት የበርካታ ንፁሃን ወገኖቻችን ህይወት እንዲጠፉና አካላቸውም እንዲጎድል አድርገዋል። ይህ በየትኛውም ዓይነት ተዋውሟዊ ስሌት ፖለቲካ ሊሆን አይችልም—ሆን ብሎ ህዝብን ለመጉዳት ሚኬር እንጂ።

ፅንፈኞች በኦሮሞ ህዝብ ደስታ የሚደሰቱና ወግና ባህሉን የሚያወቁ የፖለቲካ ነጋዴዎች ናቸው። ህዝቡ በክረምት ወስጥ ሰጥሞ ፀደይን እንዳያይ የሚሹ፣ የፀደይ ፀሐይን ሳይጠግብ በዚያው እንዲያሸልብ የሚያደርግ አጀንዳን የሰነቁ፣ አርሶ አደሩ የዘራወን እሸት ማፍራቱን እንዳያይ የፈረዱበትና የነገ ተስፋው እንዲጨልምበት የሚያሴሩ ለህዝብ የሚያስቡ ጠላቶቹ ናቸው።

ታዲያ እነዚህ ለባዕዳን በተላላኪነት ተሰልፈው ከኦሮሞ ህዝብ ወግና ባህል ጋር የሚጋጩ የገዛ ወገናቸውን የሚያባሉ ግለሰቦችንና ቡድኖችን "ኦሮሞዎች ናቸው" ብዬ ለማሰብ ይከብዳል። "ለምን?" ከተባለ፤ ፅንፈኞቹ ከኦሮሞ ወግና ባህሎች እንዲሁም እምነቶች ጋር በገሃድ የሚጋጩ ከሆነ፤ የእነዚህ አካላት ኦሮሞነት በምንም ዓይነት ስሌት ቁጥር ወስጥ ሊገባ አይችልም—ኦሮሞ ሆኖ ራሱ ከሚያምንበት ወግና ባህል ጋር በመጋጨት የራሱን ትወፊት ሊቀለብሰው ይሞክራል ተብሎ ስለሚይታሰብ ነው።

ርግጥ የተላላኪ ፅንፈኞቹ ዓላማ 'ገንዘብ እስካስገኘ ድረስ ማንኛውም የሁከት መንገድ ትክክል ነው' የሚል በመሆኑም ባህላዊም ይሁን ሃይማኖታዊ ቀኖናዎችን ከመጋፋት ወደ ኋላ ይላሉ ተብሎ አይታሰብም።

ፅንፈኞቹ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ እጅግ የሚከበሩትን አባገዳዎች እንኳን አያከብሩም። የዛሬ ዓመት ገደማ የተማለከትነው ይህንኑ ነው። አባገዳዎች ህዝቡ በግርግር እንዳይጨፈለቅ ንግግር ሲያደርጉ ተላላኪ ፅንፈኞቹ ማጋገሪያወን ከአባ ገዳዎች ላይ በገሃድ ሲነጥቁ ተስተውሏል። ይህም እነዚህ ሃይሎች ከራሳቸው ፖለቲካዊ ሴራ ውጭ የኦሮሞን ህዝብ ባህላዊ ሜዎችን አይቀበሉም። በእኔ እምነት እንዲህ ዓይነቱ ተግባር ባህልንና ታሪክን ብሎም ታላላቅ አባቶችን አለመቀበል ነው።

እንደሚታወቀው ሀገራችን በዩኔስኮ ያስመዘገበችው የገዳ ስርዓት የዴሞክራሲ ማስረትና ሁነኛ ማሳያ ነው። ረጅም ታሪክ ያለው የኦሮሞ ህዝብ የስልጣን ማሻጋገሪያ ስርዓትም ነው። የገዳ ስርዓት እንደ ማንኛወም ዘመናዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት፤ የገዳ ስርዓትም ህግ አወጪ ህግ አስፈፃሚ ህግ ተርጓሚ አካላት አሉት።

በዚህ የስልጣን ክፍፍል ማስረትም ስርዓቱ ህዝቡን በባህላዊ መንገድ ያስተዳድራል። በስልጣን ክፍፍሉ ቦታ ወስጥ አባገዳዎች ቀዳሚውን ስፍራ ይወስዳሉ። የላይኛው የስልጣን እርከን የአባገዳው ነው። እናም በየስምንት ዓመቱ አንዴ የሚሚጠው አባገዳ በማህበረሰቡ ወስጥ የሚፈጠሩ መናቻወን ተግዳሮቶችን ይፈታል፤ የሚፈቱበትን መንገዶችንም ያመላክታል።

በስርዓቱ ወስጥ የቤተሰብ፣ የጎረቤት፣ የአካባቢ ወይም የደን ጥበቃ እንዲሁም የግጭት አፈታት ስርዓት እስከ አሁን የተረጋገጡና እየተሰራባቸው የመጡ ህግጋት ናቸው። የዚህ ስርዓት ዋነኛ ተዋናይ የሆኑት አባገዳ በህብረተሰቡ ወስጥ ተሰሚነት ያላቸወና ክብር የሚቸራቸው ናቸው።

ህብረተሰቡ እርሳቸው ያሉትን ነገር በባህሉና በደንቡ ማስረት ይፈፅሙል። በአጭሩ አነጋገር አባገዳው የኦሮሞ ህዝብ ዘወግ ናቸው ማለት ይቻላል። ሁሉም የኦሮሞ ተወላጅ አክብሮትን በመቸር ለአባገዳው ወሳኔ ተገዥ ይሆናል። ፅንፈኛው ሃይል ግን ይህን ተፃርሮ በመቆም አባገዳዎችን የሚቀበል አለመሆኑን በገሃድ አሳይቷል።

ያም ሆኖ የኢሬቻ በዓል የኦሮሞ ህዝብ ወግና ባህል ማገለጫ እንዲሁም የፈጣሪ ማመስገኛና ምስጋና ማቅረቢያ በመሆኑ፤ ህዝቡ እስካለ ድረስ በየዓመቱ ይከበራል። የትኛወም ሃይል የህዝቦችን ወግና ባህል ተፃርሮ እንዲቆም ህገ መንግስቱ አይፈቅድለትም። እናም የኦሮሞ ህዝብ ወግና ባህል ማሳያ የሆነው ኢሬቻ ባህለዊ ትወፊቱን ጠብቆ ነገም ይሁን ከነገ በስቲያ መከበሩን ይቀጥላል።